# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 15

ሚያዝያ 22 ቀን 2014ዓም(30-04-2022)

የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ ስርጭት የስነጽሑፍ ክፍል ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች እንኳን ለዳግማ ትንሳኤው አደረሳችሁ በማለት መልካም ምኞቱን እዬገለጸ ፣ ለሙስሊም ኢትዮጵያን ወገኖቻችንም ኢድ ሙባራክ በማለት መልካም የኢድ በዓል እንዲሆንላቸው ከልብ ይመኛል።የእነዚህ ታላላቅ እምነት ተከታዮች የሆኑ የአንድ አገር ልጆች ለዘመናት ተሳስበውና ተቻችለው ፣አንዱ ለሌላው ቆሞ፣ክፉና ደጉን ያሳለፉ፣በቤተሰብነት ደረጃ ተዋልደውና ተዛምደው የኖሩ ፣ለአገራችን ነጻነት እኩል ዋጋ የከፈሉ፣ቢላዋ ሳይለያቸው በስማምና ቢስሚላህ ብለው ባርከው በአንድ ገበታ ላይ ቀርበው የበሉ፣ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ ሆነው የኖሩ በመሆናቸው ለዓለም ሕዝብ አብሮነትንና መቻቻልን ያስተማሩ ለመሆናቸው ረጅሙ የጋራ ታሪካቸው ይመሰክራል።ያገራችውን ጠላት በጋራ የመለሱ እንጂ ለጠላት መሣሪያ በመሆን አንዱ በሌላው ላይ አልተነሳም።ለመነሳትም የሞከረ ቢኖር በሁለቱ እምነት ተከታዮች ጥምር እርምጃ ለመቀጨት ችሏል፤አሁንም ሆነ ወደፊትም ይቀጫል።ይህ ዘመን ተሻጋሪ አንድነታቸው ለወደፊቱም ሳይበረዝ እንዲቆይ ያለንን ምኞትና ተስፋ ለመግለጽ እንወዳለን።

የትንሳኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ባለፈው ሳምንት መቅረብ የነበረበት የሥነጽሑፍ ክፍላችን ዘገባ እንደሌላው የስርጭታችን ክፍለጊዜ እንደማይቀርብ መግለጣችን ይታወሳል።በዚህ ባሳለፍነው አስራ አምስት ቀናት ውስጥ በአገራችን የተከሰተውን ሁሉ ለመፈተሽ ጊዜው ስለማይበቃ ዋና ዋና ናቸው ብለን ያሰብናቸውን ብቻ በማንሳት የዛሬውን ዘገባችንን በተወሰነለት የሰዓት ገደብ ለማጠናቀቅ እንሞክራለን።

ባለፉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ከታዘብናቸውና አነጋጋሪ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አብይ አህመድ የብልጽግና ፓርቲ አመራር የሆኑትን ሰብስቦ ስልጠና በሚል ስም አምባገነናዊ ቅላጽ በመሰለ መልኩ ያደረገው የተምታታና የማስጠንቀቂያ ዛቻ የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛል።በዚህ ስብሰባ ላይ ለእሱ ሥልጣን የማይመቹትንና በተቃዋሚነት ብቅ ብቅ በማለት ላይ ያሉትን የብዙ ጊዜ አጋሮች ሆነው የቆዩት አሁን ላይ ግን ከእንቅልፋቸው ባነውም ይሁን ከሥልጣን በመገፋታቸው ምክንያት አኩርፈው ለሥርዓቱ አናንበድድም በማለት በተለይም በሚወክሉት የአማራ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውንና ሊደርስ የታሰበውን አደጋ በማጤን ድምጻቸውን በማሰማት ላይ ያሉትን ጸጥ ለማድረግ ወይም ለማሶገድ ታስቦ ያደረገው ስብሰባ ለመሆኑ ከስብሰባው ማግስት የተወሰዱት የማውገዝና የዛቻ ጋጋታ በግልጽ አሳይቷል። በዚህ ስብሰባ ላይ የብልጽግና ፓርቲ አባላትን በሶስት ደረጃ የከፈለ ሲሆን በጨለማው ሰፈር የተሰለፉ፣ለብልጽግና ዓላማ የማይጠቅሙና እንቅፋት ብሎ የፈረጃቸው የአማራው ድርጅት የተባለው የብአዴን አሁን የአማራ ብልጽግና አመራር አባላትን ነው።ከነዚህ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት አቶ ጸጋዬ አራጌ፣አቶ ዩሃንስ ቧያለው፣አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና አቶ ንጉሡ ጥላሁን ይገኙበታል።

ይህ ስብሰባ ካለፈው የመከላከያ አባላት ከተሳተፉበት ስብሰባ ጋር ስልጠና በሚል ስም ቢመሳሰልም ምክንያቱ የተለያዬ ነበር።የመከላከያ አባላቱ ወደፊት ለሚወስዱት የታቀደ እርምጃ ፈቃድና ሙብት የሚሰጥ ሲሆን የፓርቲው አባላት ስብሰባ ግን በወታደራዊ ክንፉም ሆነ በደህንነት ሃይሉ የሚቀጡትን የሚለይበት፣ስብሰባ መሆኑ በማያሻማ መልኩ የታዬበት ነበር።ይህ ስብሰባ በደርግ ዘመን በዬቀበሌው የሚጠረጠሩ ተቃዋሚዎችን በተለይም የኢሕአፓን አባላትና ደጋፊ እንዲሁም በውስጡ የነበሩትን የደርግ አባላት ለመግደል በስብሰባ ላይ ጠቁሞ የማውጣቱን ሂደት ያስታውሰናል።ያም ሆነ ይህ በገሃድ

የሚታዬው አብይ አህመድ የአማራውን መነሳሳት በተለይም የፋኖን መደራጀት ለሚመራው የኦሮሙማ ቡድን  አገር የማፍረስ ዓላማ አለመሳካት እንደዋና ስጋትና ጠላት  ስለቆጠረው፣ያንን ሕዝባዊ መነቃቃት ለማኮላሸት የወጠነው ኦነጋዊ ሴራ መሆኑ በየእለቱ የሚፈጽመው በደልና ግፍ ይበልጥ የአብይን ማንነት እያረጋገጠው መጥቷል።ትናትናም ሆነ ዛሬ እንዳልነውና እንደምንለው አብይ አህመድና የሚመራው ድርጅት ኦሕዴድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም የሚጨነቁ ሳይሆን ለኦሮሚያ ሃገር ግንባታ ተግተው የሚሰሩ ለመሆናቸው ሌላ ማስረጃ መፈለግ አያሻም። አብይ አህመድ ኢትዮጵያን በምላሱ ኦሮሚያን በልቡ ይዞ የሚንቀሳቀስ አስመሳይና ከሃዲ ብሎም ውሸታም፣በኢትዮጵያ የመሪዎች ታሪክ ውስጥ ያልታዬ አጭበርባሪ መሪ ነው።ለሱ ትልቁ እራስ ምታት የሆነበት ፋኖ የተባለው የአማራው ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ መከታ የሆነው አገር ወዳድ ሃይል ነው።ፋኖነት አማራነት ወይም ኦርቶዶክስ ክርስቲያንነት ወይም ሙስሊምነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጥምር  ሕዝባዊ ሃይል ከዛም በላይ ሰብአዊነት ነው።ፋኖ የዛሬ ሳይሆን ካያት ቅድመአያት፣ከኢትዮጵያ ነጻነት ታሪክ ጋር አብሮ የኖረ የአገር ክብር ዘበኛ ማለት ነው።የፋኖን አገር ወዳድነት፣ የትግል ችሎታና ስልት የሌሎቹም ለነጻነታቸው ሲታገሉ የነበሩ አገሮች በምሳሌነት የሚያሞግሱትና የሚከተሉት የትጥቅ ትግል አስተማሪያቸው ነበር።ለምሳሌም የቻይናው መሪ ማኦ ሴዱንግ በሽምቁ የትጥቅ ትግላቸው ወቅት የኢትዮጵያውያን አርበኞችን  ትግል ከሚያደንቁትና ከሚያከብሩት መሪዎች አንዱ ነበሩ።በወታደራዊ የሽምቅ ትግል ስልት መመሪያቸውም እንደምሳሌ የሚያቀርቡት የኢትዮጵያን የፋኖ አርበኞችን ትግል ነበር። የኬንያው የመጀመሪያው ፕሬዚዴንትና የኬንያ አባት በመባል የሚታወቁት ጆሞ ኬንያታም በሚመሩት የነጻነት ትግል የማዎማዎ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያውያኑ የፋኖ ትግል የብርታት ሞተራቸው እንደነበር መስክረዋል።ዛሬም የትናንትናዎቹ ፋኖዎች ልጆች በዛሬው የፋኖ ትግል ውስጥ መሰለፋቸው ከደማቸው ጋር ተቀላቅሎ የወረሱት ወኔ እንጂ ለሆድና ለጥቅም በቅጥረኛነት የሚነዱበት የገዳይ፣አገር አፍራሽ ተልእኮ የሚፈጽሙበት የጥፋት ቡድን  አይደለም።የዚህ አይነቱ ወራዳ ተግባር በኦነጎች፣በወያኔና በአጋሮቻቸው ሰፈር እንጂ ፋኖ በተወለደበት መሬት ላይ አይበቅልም።ፋኖ ቤቴ ንብረቴ ወይም ልጄ ሚስቴ ፣እናቴ አባቴ ሳይል ለአገሩ ክብር በራሱ ስንቅና ትጥቅ እምቢ ለወገኔ እምቢ ለሃገሬ ብሎ ለትግል የሚሰለፍና የሚሰዋ ጀግና ነው።

ፋኖን ለትግል የገፋፋውና የሞቀ ቤቱን ጥሎ ለዱር ለገደል ያበቃው ላለፉት ሃምሳ ዓመታት በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት በአገራችን የሰፈነው አማራና ኢትዮጵያ ጠል የሆነ የጎሰኞች ሥርዓት የራሱን አገር ለማፈራረስ የተሰለፈው የህወሃትና የኦነግ ጥምረት ቡድንና ተከታዮቻቸው ከውጭ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን በንጹሃን ዜጎች ላይ የሚፈጽሙት ዘግናኝ ወንጀል ገደብዬለሽ ስለሆነ የአገሩንና የወገኑን ህልውና ለማስከበር ሲል ነው።የነዚህ ጻረ አገርና ሕዝብ ሃይሎች ትንኮሳ ካለተገደበና ድራሻቸው ካልጠፋ ኢትዮጵያ እንደ አገር ሕዝቡም እንደ ሕዝብ ተከብሮ የመኖሩ ዕድሉ የመነመነ ነው። በመሆኑም ሕዝብን እንደ ዜጋ አገርንም እንደ አገር ካላስከበረ በቀር ፋኖ ትጥቁን አይፈታም።አሁን ላይ በብዙ ሽህ የሚቆጠረው ፋኖ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሚሊዮን ያድጋል።ለዚያ ድል ግን ሁሉም አገር ወዳድ ፋኖ በመሆን በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ፣በሚችለው ሁሉ የድርሻውን ማበርከት ይኖርበታል። በጎጥና በመንደር እንዲሁም በሃይማኖት ፋኖን ለመበታተን በመንግሥት የታገዘ ሴራ ስላለ ያንን ማምከን የሁሉም ግዴታ ነው።ዓላማና እራእይ ያለው ትግል በአንድ ቦታና በተወሰኑ ሰዎች የሚጀመር ለመሆኑ ታሪክ ያረጋግጣል።በአንድ ቦታና በጥቂት ሰዎች የተጀመረ ትግል ግን እንደ ቋያ እሳት እዬተስፋፋ ብዙሃኑን እያቀፈ ይሄዳል እንጂ በቀላሉ አይከስምም።በአማራው ክልል የተጀመረው የፋኖ ትግል አገር አቀፍ ሕዝባዊ ትግል ይወልዳል።እዬወለደም ነው። በተረኝነት ያበደው የኦሮሙማ ኦነጋውያን ቡድንና ተከታዮቹ ዕድል ከተሰጣቸው ሕዝብ  ሰላምና አገር አልባ ሆኖ በውጭ ወራሪዎችና በእርስ በርስ ጦርነት ሲተራመስ መኖሩ አይቀሬ ነው።ለዛም ነው ከዚህ አደጋ ለመውጣት ሁሉም ፋኖ ይሁን የምንለው።

አብይ አህመድ የረገጠው መሬትና የዳበሰው ሰው በሰላም እንደማይኖሩ የሚታማ ሲሆን፣በአብይ የተነካ የለውም በረካ እስከመባል ድረስ የተመሰከረለት እውነት መሆኑ በተደጋጋሚ እግሩ በረገጠበት አካባቢ ተከትሎ የሚመጣው ግጭትና ግድያ፣ሁከትና ሽብር ያረጋግጣል።በሄደበት ቦታ የቀውስ ሴራ ጠንስሶ የሚመለስ መሆኑ ከዚህ በላይ ማስረጃ መፈለግ አያሻም።ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ጎንደር ሄዶ የዋግን ዞን ጎብኝቶ የአገውን ማህበረሰብ ከአማራ ማንነቱ ለመነጠል ያደረገው ሙከራ አሁን በጎንደር አካባቢ ለሚካሄደው ሰላም አልባ ሁኔታ መንደርደሪያ ሆኗል።አብይ የአገውን ማህበረሰብ ከሌላው ጎንደሬ አማራ ለመነጠል የግንባታና የቅርጻቅርጽ ኪነታዊ ችሎታ ያደነቀ መስሎ ላሊበላንና ጎንደር ከተማን የሠራችሁት እናንተ ናችሁ በማለት በነጠላ ባለቤትነት እንዲያስቡ መርዟን ጠብ አድርጓል። ይህ አባባሉ ለአገውና ለቅማንት ነጻ አውጭ ነን ባዮች የስውር ድጋፍ መልእክት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።እግረመንገዱን በከባቢው የሚንቀሳቀሰውን የፋኖ ትግል ለማምከን ከመከላከያ ሃይሉ መሪዎች ጋር ለመምከር እንደሆነም አይካድም።እግሩን ተከትሎ በፋኖ ላይ የሚወርደው ውርጅብኝ ተጠናክሮ ቀጥሏል።ከመሃል የአነግ ልጅ አሕዴድ ለጥፋቱ ሁሉ ፋኖን ተጠያቂ ከማድረግ አልቦዘነም።በተባባሪው በብአዴን በኩል ፋኖን ለመበታተንና ትጥቁን ለማስፈታት ያልተሞከረ የለም።አሁንም ሙከራው ቀጥሏል።የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ተብዬው ከፋኖም አልፎ አማራውን ጽንፈኛ የሚል ቅጥያ የሰጠው ሲሆን ፋኖንም የጽንፈኛ ሰራዊት ብሎታል።በዚህም አላቆመም የሚገባቸውን ለመስጠት ዝግጅታችንን ጨርሰናል ሲል ፎክሯል።ፉከራውም ሃይማኖትን ተገን አድርጎ በጎንደር በኩል ብቅ ብሏል። አዎ ኢትዮጵያን ለመበታተን የግድ ፋኖን ማጥፋት አስፈላጊ ነው።ነገር ግን ፋኖ በጎሰኞች ቅልብ ቅጥረኛ የሚሸነፍ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያውያን አገር ወዳዶች ጥምረት ስለሆነ ሴረኞቹ ቀድመው ይጠፋሉ።

አገር አጥፊው የህወሃት የበኩር ልጅ የሆነው አነግ/ኦሕድድ በጎሳ የሚያደርገውን መከፋፈል ወደ ሃይማኖታዊ ቅራኔና መከፋፈል አሻግሮታል። ከላይ ከፍ ብሎ እንደገለጽነው ለዘመናት በሰላምና በፍቅር የኖሩትን የአንድ አገር ልጆች ከዛም ባለፈ ቤተሰቦች ክርስቲያንና ሙስሊም በማለት ደም ለማፋሰስ ብዙ ቢሞክርም ሳይሳካለት ቆይቷል።ከሁለት ቀናት በፊት ግን ይህንን ሙከራውን በማይጠረጠረው በጎንደር ሕዝብ ላይ ፈትሾበታል።ጎንደርን እንደ ቤተ ሙከራ አድርጎ ወደ ሌላው ክፍለሃገር ለማቀጣጠል የታሰበ ሴራ መሆኑን ሁሉም አምኖበታል።ወቅትና ምክንያት አስታኮ በአንድ አገር ልጆች መካከል በተነሳው አላስፈላጊ ግጭት ብዙ ንጹሃን የሞቱና የቆሰሉ ፣የብዙ ሰላማዊ ዜጎችም ንብረት የወደመና የተዘረፈ በመሆኑ የጎንደርን ተወላጅ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ጨዋ ኢትዮጵያውያን አንገት አስደፍቷል።ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን የሞቱትን ለገነት(ለጀነት) የቆሰሉትን ለፈጣን ማገገም እንዲበቁ እዬተመኘን ለቤተሰብና ለወዳጅ በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ምስሊሞችና ክርስቲያኖች ብርታትና ብስለትን እንመኛለን።ግጭቱ የተነሳው በጎንደር ከተማ ኗሪ የነበሩት፣በሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን በክርስቲያኑ ማህበረሰብ የሚከበሩ ሸህ ከማል ለጋስ የተባሉ አባት አርፈው ለመቃብር በወጣው የሁለቱም እምነት ተከታይ በሆነው ጎንደሬ ላይ ሽብር እንዲቀሰቀስ የመቃብር ድንጋይን ምክንያት በማድረግ ሆን ብለው በተደራጁ አሸባሪዎች የተቀሰቀሰ መሆኑ ሃዘኑን የበለጠ መሪር ያደርገዋል።ድንጋይ ቀርቶ ህይወትና ኑሮውን ተካፍሎ ለሚኖረው የጎንደር ሕዝብ በዚህ ተራ ነገር ተጋጨ መባሉ ከማሳፈሩም በላይ ለሽብር ቀስቃሾቹም ትልቅ ፌስታ ነው።ከሳምንታት በፊት በተማሪዎች የተነሳውን የሶላትን ጥያቄ ምክንያት አድርገው ብጥብጥ ለማስነሳት የተሞከረ ቢሆንም በሕዝበ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ የጋራ ትግል ወደ መጥፎ አቅጣጫ ሳያመራ በጊዜው እንዲቀጭ ሆኗል።በዚያ የተበሳጩት የጥፋት ሃይሎች የሸህ ከማልን ዜና እረፍት መጠቀሚያ ካርድ ለማድረግ ሞክረዋል።

በማይረባ ለዚያውም በድንጋይ ምክንያት መጣላት ከድንጋይ ማነስን ያመለክታል።የሰው ልጅ በተለይም የጎንደር ሕዝብ በመቃብር ድንጋይ ተጋደለ ቢባል ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ለመጭውም ትውልድ ጎንደሬ

ከዛም በላይ ለመላው አማራ ሃፍረት ነው።መታዬት ያለበት የጠቡ ዓላማ ከድንጋዩ በላይ መሆኑን ነው።የጎንደሬውን አንድነት በማሻከር ያዳከሙና ፍላጎታቸውን የሚያሟሉ የሚመስላቸው ከድንጋይ ያነሱ የአስተሳሰብ ድኩማኖች፣እኩይ አገር የማፈራረስ ዓላማ እንዳይሳካላቸው ከነሱ በላይ ሆኖ መገኘት ተገቢ ነው።ጎንደርን ለማዳከም በተለያዩ መንገዶች ጥረት ተደርጓል፤የወልቃይትና ጠገዴን ለም መሬት ወያኔ እንዲወስድ፣ በጎንደሬነት ብቻ ሳይሆን በአማራነት አብረው የኖሩትን የቅማንትና የአገው ማህበረሰብን ለብቻቸው ገንጥሎ ለአደጋ እንዲጋለጡና ለኦሮሙማው ስልቀጣ ምቹ ማድረግ፣ ለአማራው ሕዝብ ተቆርቋሪና መሪ እንዳይኖረው ፣ለሙብቱ ተከራካሪና ጠበቃ ብሎም ጠላት ሲያጠቃው ተፋላሚ የሆነው ፋኖና ልዩ ሃይሉ እንዳይደራጅና እንዲበታተን በማሴር ብዙ ተሞክሯል፤ አሁንም እዬተሞከረ ነው። ያለው መፍትሄ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ያም ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል የሚለውን የአበው አባባል እንደምክር ወስዶ በፋኖ መካከል ንፋስ እንዳይገባ ቀዳዳውን በህብረት አጥር መድፈን ነው።

የህወሃትና አነጋውያን የሽብር ተላላኪዎች በሙስሊሙ ስም የክርስቲያኑና የሙስሊሙን የአማራ ፋኖ ለማጥቃት ጽንፈኛና ሴባ የሚል የስድብ ናዳ ሲወረወር መስማቱ ሁኔታውን ለማባባስ ምን ያህል እርቀት መኬዱን ያሳያል።በተለይም የአማራ ክልል እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ቀድሞ የታቀደ ጭፍጨፋ ነው በማለት ጣቱን ወደክርስቲያኑና ፋኖ ሲጠቁም በግጭቱ የሁለቱም እምነት ተ,ታዮች መሞታቸውን በመሸፋፈን ጥቃቱ በሙስሊሙ ብቻ ላይ እንደደረሰ አድርጎ በማስቀመጥ የሴራው አካልነቱን አሳይቷል። አዲስ አበባ የሚኖረው ጥቂት የማይባል ሙስሊምም በተዛባ ቅስቀሳ በታላቁ አንዋር መስጊድ ግቢ ውስጥ ባካሄደው ተቃውሞ ቀውሱን የማጋጋል ሂደት ተስተውሏል።በዛም ኦሕዴድ በፋኖ ላይ ያወረደው ስድብና ትችት በሙስሊሙ ተሰብሳቢ ሲደገም ተደምጧል።ይህ የወያኔ፣ የኦሕዴድና አነግ ሴራ ከሰሞኑ የአብይ አህመድ፣አዳነች አቤቤ፣ሽመልስ አብዲሳ፣ለማ መገርሳ፣ጃንማሮና ሌሎቹም አነጋውያን ያደረጉትን ድብቅ ስብሰባ ተከትሎ የመጣ የሽብር ውሳኔ ለመሆኑ ብዙዎች ይናገራሉ።እኛም ጥርጥር የለንም። የነውጠኞቹ መሪ ጁዋር ሞሃመድም ከደሙ ነጻ ነው አይባልም። ሁኔታው ከመከሰቱ በፊት በሳውዲ አረቢያ በኩል ወደ አሜሪካ መሄዱና ለሙስሊሙ ያስተላለፈው የሽብር ጥሪ የአነጋውያኑ ጥምረት የለኮሰው እሳት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው። በተለይም ለቀውሱ ፋኖን ተጠያቂ ማድረጉና መኮነኑ ከቤተመንግሥቱ የሴራ ምንጭ የተቀዳ ለመሆኑ የተስተጋባው መፈክርና እርግማን ተመሳሳይነት ያረጋግጣል።

በውስጥና በውጭ ያሉት አክራሪ አነጋውያን በሙስሊሙ የሙብት ጥያቄ ሽፋን የግብጾችንና የሌሎቹንም ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ዓላማ ለማስፈጸም ተነስተዋል። አብይ አህመድና የሚመራው መንግሥትም ለደረሰው የህይወት መጥፋትና የእምነት ቦታዎች መውደም ደንታ አልሰጠውም።በደቡብ ክልል በስልጢ ወረዳ አክራሪ ሙስሊሞች የኦርቶዶክስንና የፕሮቴስታንትን ቤተክርስቲያናትን ሲያቃጥሉን ሲዘርፉ መንግሥት ተብዬው ቀድሞ ቢነገረውም ሊከላከል ፈቃደኛ አልሆነም።ሌላው ቀርቶ በተቀመጠበት ከተማ በአዲስ አበባ የልደታ ቤተክርስቲያንን ለማውደም አክራሪ ሙስሊሞች ሆ ብለው አስፋልት ሞልተው ሲመጡ ያስቆማቸው የመንግሥት የጸጥታ አካል አልነበረም።ሕዝቡ ከዬቤቱ ተጠራርቶ ባደረገው መከላከል የአክራሪዎቹ ዓላማ ሳይሳካ ቀርቷል።ይህ ማለት ግን ዳግም አይሞከሩም ማለት አይደለም።በስልጢ ወረዳ ለደረሰው ውድመት መሪና አቀነባባሪ የሆነውም የከባቢው የጸጥታ ክፍል ሃላፊ የሆነው ኮሚሽነር መሆኑ ታውቋል።በተመሳሳይ በሐረር፣ድሬዳዋ፣በጅጅጋ፣በጅማ አክራሪዎች ያደረጉት የማውደም ዘመቻ ለጊዜው ሊገታ ችሏል።ታዲያ ይህ ሁሉ ሲሆን መንግሥትና ሕግ አስከባሪ አለ ብሎ ለማለት አያስደፍርም።ከሃምሳ ሽህ በላይ ፖሊስ ተቀጠረ በተባለባት በአዲስ አበባ ከተማ 500 የማይሞሉ አክራሪ አሸባሪዎች ያሻቸውን ለማድረግ ተጠራርተው በግልጽ ሲሰማሩ ሕጉና ሥርዓቱ ለማንና ለምን እንደቆመ ማሳያ ነው።

ተመሳሳይ እኩይ ድርጊት በሌሎቹ ክፍላተ ሃገር በተለይም በወሎ፣በጎጃም፣በሸዋ፣...ወዘተ እንዳይከሰት ነቅቶ መጠበቅ ተገቢ ነው።አትዮጵያ ከበቂው በላይ ችግር አለባት ፤ሌላ ችግር አትሻም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፣የሰላም እጦቱ፣ስደቱ፣ በማንነቱ መገደሉ፣መፈናቀሉ፣መዘረፉ፣ሳያንሰው በሃይማኖት ልዩነት እንዲጋደል ማድረጉ የወንጀል ወንጀል ነው።በነዚህ ድክመቶች ጀግንነት አይታይም፤የሚታዬው አውሬነትና ኋላ ቀርነት ብቻ ነው።

የኑሮ ውድነቱ ከሚችሉት በላይ ሆኖ በሥልጣን ላይ የተቀመጠው አገር ጠሌ የጎሰኞች ስብስብ አባል የሆነ ከአጫፋሪዎቹ ጋር  አንድ በሬ በ200 ሽህ ብር ገዝቶ ሲበላ ሰፊው ሕዝብ እንጀራ በሽሮ ለመብላት አቅም አጥቷል።የሰሞኑ የፋሲካ በዓል ገበያ ያሳዬው ቢኖር የበሬ የፍዬልና የበግ ሥጋ ለመብላት አለመቻልን ብቻ ሳይሆን ዶሮና እንቁላልም ብርቅዬና ቅንጡ ምግቦች እዬሆኑ መምጣታቸውን ነው። ሌላው ቀርቶ ጎመን ለመብላትም ቢሆን ከማሳው እዬተባረረ፣በቦታው የቀረውም  ዝናብና ሰላሙ እንደመሪዎቹ ስለከዳው አምርቶ መብላት አልቻለም።ከበርቴ ሲበላ የደሃው ባዶ ሆድ ሲጮህ በጥጋብ የሚያገሳ የሚመስላቸው ጨካኞች ለአስረሽ ምችው ኑሯቸው ገደብ ካላበጁለት እንደ ዶሮዋ  በጭድ የሚለበለቡበት ሕዝባዊ አመጽ አይቀሬ ነው።ያም እንዳይደርስባቸው ነው ሕዝቡን በሆነ ባልሆነው እዬለያዩ እርስ በርሱ የሚያጋጩት።

አሁንም እንላለን ሕዝብ ሆይ ለመኖር አገርና ሰላም ፣ለማደግና ለመሻሻልም መብትና ነጻነት ወሳኝ ነው።የነዚህ እሴቶች ባለቤት ካልሆንክ ኑሮህ የሲኦል  ወይም የገሃነም ኑሮ ይሆናል።ከዚያ ለመገላገል ወሳኙ አንተ ነህ፤መንገዱም ተባብረህ መታገል ብቻ ነው። በውጭ አገር እርዳታ አትተማመን።የውጭ እርዳታ ተቀባይ ሆኜ እኖራለሁ ካልክ ነጻነትህን በሆድህ የሸጥክ የዘላለም ባሪያ ትሆናለህ።አገርህንም አስረክበህ አገር አልባ ትሆናለህ።ለባዕዳን ያደሩ፣በባዕዳን ሳንባ የሚተነፍሱ አስመሳዮችም እንዳያታልሉህና ትግልህን እንዳይቀለብሱት ነቅተህ ጠብቅ።ችግር ከሚያስድድህ የችግር ምንጩን አሳደህ ብትደፍነው ይመረጣል።በአገርህ ኩራ!በራስህ ተማመን!በጎሳ ማንነት ከፋፍለው ሲያጫርሱህ ያልረኩት ጨካኞች አሁን ደግሞ በእምነትህ ከፋፍለው ሊያጫርሱህ ጀምረውታልና ካለፈው ተምረህ እምቢ በል።የማንኛውም እምነት አስተምሮ ፍቅር፣ደግነት መተሳሰብ እንጂ አውሬነትና ጥላቻ አይደለም።በሰው ልጅ ደም መፍሰስ፣በስቃይና መከራ  የምትረካ ከሆነ የሰይጣን ጭፍራ እንጂ የፈጣሪ ተከታይ አትሆንም። ለምትገፋው የኑሮ ሸክም፣ለሰላም እጦትህ፣ለሁሉም ስቃይ የዳረገህ ሥልጣኑን የተቆጣጠረው አገር ጠል የጎሰኞች ስብስብ ነው።መሪው አብይ አህመድ ብቻውን ቢወገድ ለውጥ ይመጣል ብለህ አታስብ።መለስ ቢሄድ፣ተመስገን፣ተመስገን ቢሄድ አብይ ቢመጣ ለውጥ የለም። የግለሰቦቹ መሽጋሸግና መቀያዬር ብቻ እንጂ ለውጥ አልመጣም።አሁንም አብይን በሌላ ግለሰብና ቡድን ልለውጥ ብትል ለውጥ አታገኝም።ለውጥ ማለት መሠረታዊና ስር ነቀል ሲሆን ብቻ ነው።ጎሰኝነትን የሚጠዬፍ ፣አገራዊና ሕዝባዊ የሆነ ፖለቲካ መስመር የሚከተል ከሆነ ብቻ ለውጥ መጣ ማለት ይቻላል።ለዚያም ለዘላቂ ሰላምህና ለተሻለ ኑሮ፣ ለአገርህ አንድነት ይህንን እኩይ ስብስብ ማሶገድና የአንተ፣በአንተ፣ለአንተ የሆነ ኢትዮጵያዊ የሆነ አገር ወዳድ መንግሥትና ፍትሐዊ ስርዓት ስትመሠርት ብቻ ነው።ለዚያ ምከር ዝከር፣ተደራጅ!!

ኢትዮጵያ ከጎሳና ከሃይማኖት በላይ ናት!!

የሰውነት መንፈስ በሁላችንም ዘንድ ይደር!!